| | |
|---|---|
| ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ<br>አውቃፍ ሚኒስትር | ሰፈር 19/1440 ሂ.<br>ኦክቶበር 18/2019 ግ. |

# አላህን ማውሳትና ለሰው ልጅ መንፈስ ቀጥተኛነት ያለው አስተዋጽኦ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{الَّذِينَ آمَنُوا وَتَطْمَئِنُّ قُلُوبُهُم بِذِكْرِ اللَّهِ أَلَا بِذِكْرِ اللَّهِ تَطْمَئِنُّ الْقُلُوبُ}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው ትርጉሙም ((እነሱም) እነዚያ ያመኑ ልቦቻቸውም አላህን በማውሳት የሚረኩ ናቸው፡፡ ንቁ! አላህን በማውሳት ልቦች ይረካሉ፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

አላህ(ዐ.ወ.) ባሮቹ እሱን ማስታወስ እንዲያበዙ አዟል፡፡ በሱም ታላቅ ምንዳ እንደሚሰጣቸው እንድህ በማለት ቃል ገብቶላቸዋል፡

**{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اذْكُرُوا اللَّهَ ذِكْرًا كَثِيرًا *وَسَبِّحُوهُ بُكْرَةً وَأَصِيلًا}**

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ብዙ ማውሳትን አውሱት፡፡ በቀኑ መጀመሪያና መጨረሻም አጥሩት፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም በሌላ አንቀጽ እንድህ ይላል፡

**{وَالذَّاكِرِينَ اللَّهَ كَثِيرًا وَالذَّاكِرَاتِ أَعَدَّ اللَّهُ لَهُمْ مَغْفِرَةً وَأَجْرًا عَظِيمًا}**

ትርጉሙም (አላህን በብዙ አውሺዎች ወንዶችና አውሺዎች ሴቶችም፣ አላህ ለእነርሱ ምሕረትንና ታላቅን ምንዳ አዘጋጅቶላቸዋል፡፡) ማለት ነው፡፡ በሌሎችም አንቀጾች እንድህ ብሏል፡

{إِنَّمَا الْمُؤْمِنُونَ الَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ اللَّهُ وَجِلَتْ قُلُوبُهُمْ وَإِذَا تُلِيَتْ عَلَيْهِمْ آيَاتُهُ زَادَتْهُمْ إِيمَانًا وَعَلَى رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ *الَّذِينَ يُقِيمُونَ الصَّلَاةَ وَمِمَّا رَزَقْنَاهُمْ يُنْفِقُونَ *أُولَئِكَ هُمُ الْمُؤْمِنُونَ حَقًّا لَهُمْ دَرَجَاتٌ عِنْدَ رَبِّهِمْ وَمَغْفِرَةٌ وَرِزْقٌ كَرِيمٌ}

ትርጉሙም (ፍጹም ምእምናን እነዚያ አላህ በተወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚፈሩት፣ በነሱም ላይ አንቀጾቻችን በተነበቡ ጊዜ እምነትን የሚጨምሩላቸው፣ በጌታቸውም ላይ ብቻ የሚመኩት ናቸው፡፡ እነዚያ ሶላትን ደንቡን አሟልተው የሚሰግዱ ከሰጠናቸውም ሲሳይ የሚለግሱ ናቸው፡፡ እነዚያ በእውነት አማኞች እነሱ ብቻ ናቸው፡፡ ለእነሱ በጌታቸው ዘንድ ደረጃዎች ምህረትና የከበረ ሲሳይም አላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ህዝቦቻቸው አላህን በብዛት እንዳዎሱ እንድህ በማለት ገፋፍተዋል፡ (ንቁ ከሥራዎቻችሁ እጅግ መልካም፣ ከንጉሳችሁ ዘንድ በጣም ጥሩ፣ ከፍተኛ ደረጃ የሚያስገኝ እንድሁም ወርቅና ብር ምጽዋት ከመስጠት የበለጠና ከጠላታችሁ ጋር ተጋጥማችሁ አንገታቸውን የምትመቱና አንገታችሁን የሚመቱ ከመሆን የበለጠ የሆነውን ልንገራችሁ፡፡) ባልደረቦችም ይሁን ይንገሩን ያላህ መልክተኛ ሆይ! አሉ፡፡ እሳቸውም (አላህን ማውሳት ነው) አሉ፡፡ አንድ ሰውዬ ወደነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) መጥቶ ያላህ መልክተኛ ሆይ! የእስልምና ህግጋት በጣም በዙብኝ፡፡ ከነሱ አጥብቄ የምይዘውን ነገር ንገሩኝ ባለ ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (ምላስህ አላህን በማውሳት ከእርጥብነት አይወገድ) ነበር ያሉት፡፡

አላህን ማውሳት ታለቅ ቦታ የሚሰጠው፣ በቀላል የሚፈጸምና ትሩፋቱ ቁጥር ስፍር የሌለው ኢባዳ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ (ከርሳቸው አላህ ይወደድና) አቡ ሰዒዲኒል ኹድሪ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹ከእለታት አንድ ቀን (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሙዓዊያ መስጊድ ሲገቡ ሰዎች ተሰባስበው ተቀምጠው አዩ፡፡ ምንድን ነገር ነው እዚህ እንዲትቀመጡ ያደረጋችሁ? ሲሉም ጠየቁ፡፡ እነሱም አላህን ለማውሳት ነው የተቀመጥነው በማለት መሱ፡፡ እሳቸውም በአላህ ይሁንባችሁ እሱ እንጂ ሌላ ነገር አላስቀመጣችሁም? አሉ፡፡ እነሱም በአላህ ይሁንብን እሱ እንጂ ሌላ ነገር አላስቀመጠንም አሉ፡፡ እኔኮ ያስማልኳችሁ እናንተን በመጠራጠር አይደለም፡፡ ከአላህ መልክተኛ ዘንድ በኔ ደረጃ ካለ ሰው ከርሳቸው የሚያወራው ሐዲስ ከኔ ያነሰ የሆነ ሰው የለም፡፡ የአላህ መልክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) አንድ ቀን ባልደረቦቻቸው መስጊድ ተስብስበው አገኙ፡፡ (እዚህ ምን አስቀመጣችሁ?) ሲሉም ጠየቁ፡፡ እነሱም አላህን ለማውሳት፣ ለእስልምና ስለመራንና እሱንም ሰለለገሰን ልናመሰግነው ነው የተቀመጥነው አሉ፡፡ እሳቸውም (በአላህ ይሁንባችሁ ይሃችሁ እንጂ ሌላ ነገር አላስቀመጣችሁም?) ሲሉ ጠየቁ፡፡ እነሱም በአላህ ይሁንብን እሱ እንጂ ሌላ ነገር አላስቀመጠንም አሉ፡፡ እሳቸውም (እኔኮ እናንተን በመጠራጠር አደለም ያስማልኳችሁ፡፡ ነገር ግን ጅብሪል ወደኔ መጥቶ አላህ (ዐ.ወ.) በናንተ መላእክት ዘንድ እንደሚፎክርባችሁ ስለነገረኝ ነው) አሉ፡፡

አላህን የማውሳት ቃል የልቦች ሕይወትና አላህ (ዐ.ወ.) ዘንድ እጅጉን የተወደደ ቃል ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሙሳ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ አሉ፡ ( ጌታውን የሚያወሳና ጌታውን የማያወሳ ሰው ምሳሌ እንደ ሕያውና ሙት ሰው ነው)፡፡ ሙስሊም ባወሩት ሌላ ቃል ደግሞ እንድህ ብለዋል፡ (አላህ የሚወሳበት ቤትና አላህ የማይወሳበት ቤት ምሳሌ እንደሕያውና ሙት ሰው ምሳሌ ነው)፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ዘር የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹አንደቀን ታመው እያለ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ሊጠይቋቸው በመጡ ጊዜ ከእናትና አባቴ የማስቀደመዎት ያአላህ መልክተኛ ሆይ! ከአላህ (ዐ.ወ.) ዘንድ እጅግ ተወዳጅ የሆነው ቃል የተኛው ነው በማለት በጠየቁ ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ በማለት መለሱ፡ (አላህ ለመላእክቱ የመረጠው፡

( سُبْحَانَ رَبِّي وَبِحَمْدِهِ، سُبْحَانَ رَبِّي وَبِحَمْدِهِ)

የሚለውን ቃል ነው፡፡) (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሰሙራህ ኢብን ጁንዱብ ደግሞ ነብያችን አንድህ ማለታቸውነ እውረተዋል፡ (አላህ ዘንድ እጅጉን የተወደዱት አራት ቃላት ናቸው፡፡

سُبْحَانَ اللهِ، وَالْحَمْدُ لِلَّهِ، وَلَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ، وَاللهُ أَكْبَرُ )

በማንኛቸውም ብትጀመር የሚጎዳህ ነገር የለም፡፡) ከእለታት አንድ ቀን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (አግላዮች ቀዳሚዎች ሆኑ) አሉ፡፡ ባልደረቦችም የአላህ መልክተኛ ሆይ! አግላዮች እነማን ናቸው? ሲሉ ጠየቁ፡፡ እሳቸውም (አነዚያ አላህን ብበዛት የሚያወሱ ወንዶችና አላህ በብዛት የሚያወሱ ሲቶች ናቸው) በማለት መለሱ፡፡ በመሆኑም ነብያችን ሙዓዝ ለተባሉት ባልደረባቸው ያስተላለፉት ምክር አላህን ማውሳት ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ አሏቸው፡ (ሙዓዝ ሆይ! እኔ በአላህ ይሁንብኝ እወድሃለሁ) ሙዓዝም ከአባትና እናቴ የማስቀድምሁ የአላህ ምልክተኛ ሆይ! እኔም በአላህ ይሁንብኝ እወደዎታለሁ አሉ፡፡ ያን ጊዜ ነብያችን (ሙዓዝ ሆይ! አደራ የምልህ ነገር ቢኖር በየስግደት መጨረሻ፡

(اللَّهُمَّ أَعِنِّي عَلَى ذِكْرِكَ وَشُكْرِكَ وَحُسْنِ عِبَادَتِكَ) .

ማለትን እንዳትተው) አሉ፡፡ ትርጉሙም ‹ጌታዬ ሆይ! አንተን በማስታወስ በማመስገንና ኢባዳህን በማሳመር ረደኤትህ ከኔ ጋር ይሁን፡፡ ማለት ነው፡፡

አላህ (ዐ.ወ.)ን ማውሳት አንድን ባሪያ በማንኛውም ቦታና ጊዜ የማይለይ ኢባዳ ነው፡፡ አንድ ሙስሊም በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ እንዲፈጽመው የታዘዘ መሆኑን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት አስታውሷል፡

{إِنَّ فِي خَلْقِ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَاخْتِلَافِ اللَّيْلِ وَالنَّهَارِ لَآيَاتٍ لِّأُولِي الْأَلْبَابِ * الَّذِينَ يَذْكُرُونَ اللَّهَ قِيَامًا وَقُعُودًا وَعَلَىٰ جُنُوبِهِمْ}

ትርጉሙም(ሰማያትንና ምድርን በመፍጠር ሌሊትና ቀንንም በመተካካት ለባለ አእምሮዎች በእርግጥ ምልክቶች አሉ፡፡ እነርሱም) እነዚያ ቆመው፣ ተቀምጠውም፣ በጎኖቻቸው ተጋድመውም አላህን የሚያወሱ... ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

የማንኛውም ሙስሊም ሕይወት ሁሉም አላህን በማስታወስ የተሞላ ነው። አላህን ማስታወስ በኢባዳው ሁሉ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ለምሳሌ ስግደት አላህን ማስታወስ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَأَقِمِ الصَّلَاةَ لِذِكْرِي}

ትርጉሙም (ሶላትንም (በእርሷ) እኔን ለማውሳት ስገድ።) እንድሁም አንድህ ይላል፡

{وَأَقِمِ الصَّلَاةَ إِنَّ الصَّلَاةَ تَنْهَى عَنِ الْفَحْشَاءِ وَالْمُنْكَرِ وَلَذِكْرُ اللَّهِ أَكْبَرُ}

ትርጉሙም (ሶላትንም ደንቡን ጠብቀህ ስገድ። ሶላት ከመጥፎና ከሚጠላ ነገር ሁሉ ትከለክላለችና። አላህንም ማውሳት ከሁሉ ነገር በላጭ ነው፤ አላህም የምትሠሩትን ሁሉ ያውቃል።) ማለት ነው።

ይህን ማለትም ስግደት ሁለት ተላላቅ አላማዎች አሏት ማለት ሲሆን የመጀመሪያው ከሚጠላ ነገር የምትከልክል መሆና ሁለተኛው ደግሞ አሷ አላህን ማስታወስ መሆኗ ነው። እሱም ታላቁና ከፍተኛው የስግደት አላማ ነው።

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ማንኛውም ሙስሊም ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ የሆኑን በርካታ የአላህ ማውሻ ቃላትን ደንግገውልናል። (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ሌሊት በሚነጋ ጊዜ እንድህ ይሉ ነበር፡

(اللَّهُمَّ بِكَ أَصْبَحْنَا ، وَبِكَ أَمْسَيْنَا ، وَبِكَ نَحْيَا ، وَبِكَ نَمُوتُ ، وَإِلَيْكَ النُّشُورُ)

ቀኑ ሲመሽ ደግሞ

(اللَّهُمَّ بِكَ أَمْسَيْنَا ، وَبِكَ أَصْبَحْنَا ، وَبِكَ نَحْيَا ، وَبِكَ نموت ، وإليك المصير)

በሌላ ሐዲስ ደግሞ ሌሊቱ በሚነጋ ጊዜ

(اللَّهُمَّ مَا أَصْبَحَ بِي مِنْ نِعْمَةٍ أَوْ بِأَحَدٍ مِنْ خَلْقِكَ فَمِنْكَ وَحْدَكَ لَا شَرِيكَ لَكَ ، لَكَ الْحَمْدُ ، وَلَكَ الشُّكْرُ)

የሚል ሰው የዚያን ቀን ምስጋና ያደረሰ ሆናል። ቀኑም ሲመሽ ይህን ያለ የዚይን ሌሊት ምስጋና ያደረሰ ሆናል) ብለዋል። እንድ ሰው ቀኑን አላህን በማውሳት እንድሁም ሌሊቱን አላህን በማውሳት መጀመሩ እጅጉን መልካም ተግባር ሲሆን በመካከል ያለውንም ጊዜ አላህን በማውሳት እንዳሳለፈ ይቆጠራል።

እንድሁም አንድ ሰው ከቤት ሲወጣና ሲገባ የሚያደርሳቸው አላህን ማውሻ ቃላት አሉ። ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ማላታቸው ተወርቷል። አንድ ሰው ከቤቱ ሲወጣ፡

(بِسْمِ اللَّهِ توكَّلْتُ عَلَى اللَّهِ ، وَلا حوْلَ وَلا قُوةَ إلاَّ بِاللَّهِ)

ያለ ሰው ቅኑን መንገድ ተመራህ፣ ከተንኮልም ተበቃህ፣ ከደባም ተጠበቅህ፣ ይባላል፡፡ ሰይጣንም ከሱ ያገላል፡፡) (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኡሙ ሰለማህ እንድህ ብለዋል፡ ነብያችን ከኔ ቤት አይናቸውን ወደሰማይ ከፍ አድርገው እንድህ ሳይሉ ውጥተው አያውቁም፡

**(اللَّهُم اني أعوذُ بِكَ أن أَضِلَّ أو أُضَلَّ، أو أَزِلَّ أو أُزَلَّ، أو أَظْلِمَ أو أُظلَم، أو أجهَل أو يُجْهَل عَلَىَّ)**

እቤት ስንገባ የምንለው የአላህ ማውሳትን አስመልከቶ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ አንድ ሰው ከቤቱ ሲገባ እንድህ ይበል፡

(اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ خَيْرَ الْمَوْلَجِ ، وَخَيْرَ الْمَخْرَجِ ، بِسْمِ اللَّهِ وَلَجْنَا ، وَبِسْمِ اللَّهِ خَرَجْنَا ، وَعَلَى اللَّهِ رَبِّنَا تَوَكَّلْنَا)

ከዚያም ለቤተሰቡ ሰላምታ ይበል፡፡) እንድሁም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (አንዳችሁ በየቀኑ አንድ ሺህ መልካም ሥራ መስራት ያቅጠዋልን? )አሉ፡፡ አብረው ተቀምጠው ከነበሩት ሰዎች አንደኛው አንዳችን አንድ ሺህ መልካም ሥራ እንዴት ሊሠራ ይችላል? ሲል ጠየቀ፡፡ እሳቸውም (መቶ ጊዜ አላህን በማጥራት አንድ ሺህ መልካም ሥራ ይመዘገብለታል እንድሁም አንድ ሺህ ኃጢአት ይነሳለታል) አሉ፡፡ እንድሁም በምንበላና በምንጠጣ ጊዜ በመጀመሪያ በአላህ ስም ማለትና በመጨረሻም ለአላህ ምስጋና ማቅረብና የመሳሰሉ አላህን የምናወሳባቸው ቃላት አሉ፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዑመር ኢብን አቢ ሰለማህ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹አንድ ቀን ህፃን ሆኘ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እያሳደጉኝ ሳለ ምግብ ስንበላ እጄ ትሪውን በሙሉ ትቃኝ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ የአላህ መልክተኛ እንድህ አሉኝ (አንተ ልጅ ሆይ! በአላህ ስም ብለህ ጀምር፣ በቀኝ እጅህ ተመገብ፣ ባንተ በኩል ካለውም ተመገብ)፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ተመግበው ሲጨርሱ እንድህ ይሉ ነበር፡

(الْحَمْدُ لِلَّهِ الَّذِي أَطْعَمَنَا ، وَسَقَانَا ، وَجَعَلَنَا مُسْلِمِينَ) .

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ወደገበያም ስንገባ አላህን የምናወሳባቸው ቃለት እንድህ በማት ደንግገውልናል፡ አንድ ሰው ወደገበያ ሲገባ

(لا إِلَهَ إِلَّا اللَّهُ وَحْدَهُ لا شَرِيكَ لَهُ ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ ، يُحْيِي وَيُمِيتُ ، وَهُوَ حَيٌّ لا يَمُوتُ ، بِيَدِهِ الْخَيْرُ كُلُّهُ ، وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ)

ያለ ሰው አላህ እልፍ አላፍ መልካም ሥራ ይመዘግብለታል፣ እንድሁም እልፍ አላፍ ወንጀልን ያብስለታል በጀነትትም ቤት ይሠራለታል) እንድሁም አንድ ሰው የሚያስደስት ነገር በሚያይበት ወቅት ‹አላህ ያለው ሆነ፡፡ በአላህ እገዛ ቢሆንጂ ኃይል የለም ልንል ይገባል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{ولولا إذ دخلت جنتك قلت ما شاء الله لا قوة إلا بالله}

ትርጉሙም («አትክልትህንም በገባህ ጊዜ አላህ የሻው ይኾናል፤ በአላህ ቢኾን እንጂ ኀይል የለም፤ አትልም ኖሯልን...) ማለት ነው፡፡

አንድሁም አንድ ሰው መከራ የደረሰባቸውን ሰዎች በሚያይ ጊዜ በምስጢር አላህን ሊያወሳና ከዚያ መሰል መከራም ስለሰወረው እሱን ሊያመሰግን ይገባል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (የአንድ መከረኛ ስቃይ አስደንግጦት ‹ለአንተ ከሰጠው መከራ ለአዳነኝና ከብዙኃን ፍጥረታቱ ማብለጥን ለአበለጠኝ ለአላህ ምስጋና ይገባው፡ ፡ ያለሰው ምንም ይሁን ምን ከዚያ ዓይነት መከራ ይጠበቃል፡፡) እንድሁም አንድ ምእምን በራሱ ላይ ጭንቀት ሲደርስበት ጌታውን በማውሳት ወደሱ ይጠጋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንድህ ብሏል፣

وَذَا النُّونِ إِذ ذَّهَبَ مُغَاضِبًا فَظَنَّ أَن لَّن نَّقْدِرَ عَلَيْهِ فَنَادَىٰ فِي الظُّلُمَاتِ أَن لَّا إِلَٰهَ إِلَّا أَنتَ سُبْحَانَكَ إِنِّي كُنتُ مِنَ الظَّالِمِينَ * فَاسْتَجَبْنَا لَهُ وَنَجَّيْنَاهُ مِنَ الْغَمِّ وَكَذَٰلِكَ نُنجِي الْمُؤْمِنِينَ}

ትርጉሙም (የዓሳውንም ባለቤት ተቆጥቶ በኼደ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ በእርሱም ላይ ፈጽሞ የማንፈርድበት መኾናችንን ጠረጠረ፡፡ (ዓሳም ዋጠው)፡፡ በጨለማዎችም ውስጥ ኾኖ ከአንተ በቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ጥራት ይገባህ፡፡ እኔ በእርግጥ ከበዳዮቹ ነበርኩ በማለት ተጣራ፡፡ ለርሱም ጥሪውን ተቀበልነው፡፡ ከጭንቅም አዳነው፡፡ እንደዚሁም ምእመናንን እናድናለን፡፡) ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ጭንቅ ሲያጋጥማቸው እነድህ ይሉ ነበር፡

(لا إِلَهَ إِلَّا اللَّهُ العَظِيمُ الحَلِيمُ ،لاَ إِلَهَ إِلَّا اللَّهُ رَبُّ السَّمَوَاتِ وَالأَرْض ، وَرَبُّ العَرْش العَظِيم) .

ከፍ ሲል ያየናቸው ነብያችን አላህን ማውሻ እንድናደርጋቸው የደነግጉልን ቃላቶች ናቸው፡፡ እነሱንም ዘወትር የአላህ ማውሻ ያደረገ ሰው ቅኑን መንገድ ይመራል፣ ከዝንጋታም ይድናል፡፡ ከሰይጣንም ይጠብቁታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{اللَّهُ نَزَّلَ أَحْسَنَ الْحَدِيثِ كِتَابًا مُتَشَابِهًا مَثَانِيَ تَقْشَعِرُّ مِنْهُ جُلُودُ الَّذِينَ يَخْشَوْنَ رَبَّهُمْ ثُمَّ تَلِينُ جُلُودُهُمْ وَقُلُوبُهُمْ إِلَى ذِكْرِ اللَّهِ ذَلِكَ هُدَى اللَّهِ يَهْدِي بِهِ مَنْ يَشَاءُ وَمَنْ يُضْلِلِ اللَّهُ فَمَا لَهُ مِنْ هَادٍ}**

ትርጉሙም (አላህ ከዜና ሁሉ መልካምን፣ ተመሳሳይ፣ ተደጋጋሚ የኾነን መጽሐፍ አወረደ፡፡ ከእርሱ (ግሣጼ) የእነዚያ ጌታቸውን የሚፈሩት ሰዎች ቆዳዎች ይኮማተራሉ፡፡ ከዚያም ቆዳዎቻቸውና ልቦቻቸው ወደ አላህ (ተስፋ) ማስታወስ ይለዝባሉ፡፡ ይህ የአላህ መምሪያ ነው፡፡ በእርሱ የሚሻውን ሰው ይመራበታል፡፡ አላህም የሚያጠመው ሰው ለእርሱ ምንም አቅኚ የለውም፡፡) ማት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ብሏል፡

{ وَاذْكُرْ رَبَّكَ فِي نَفْسِكَ تَضَرُّعًا وَخِيفَةً وَدُونَ الْجَهْرِ مِنَ الْقَوْلِ بِالْغُدُوِّ وَالْآصَالِ وَلَا تَكُنْ مِنَ الْغَافِلِينَ}

ትርጉሙም (ጌታህንም በምስጢር ተዋድቀህና ፈርተህ ከጩኸት በታችም በኾነ ቃል በጧትም በማታም አውሳው፡፡ ከዘንጊዎቹም አትኹን፡፡) ማለት ነው፡፡ አሁንም እንድህ ይላል፡

{ وَمَنْ يَعْشُ عَنْ ذِكْرِ الرَّحْمَنِ نُقَيِّضْ لَهُ شَيْطَانًا فَهُوَ لَهُ قَرِينٌ}.

ትርጉሙም (ከአልረሕማን ግሣጼ (ከቁርኣን) የሚደናበርም ሰው ለእርሱ ሰይጣንን እናስጢጋለን፡፡ ስለዚህ እርሱ ለእርሱ ቁራኛ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

*   *   *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በሰዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

አላህን ማውሳት የነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች በተግባር ያሳዩት የነበረ የሕይወት ስርኣት ነበር፡፡ በዚያን ወቅት ማህበረሰቡ አላህን በመቆጣጠርና ወሰን ከማለፍ በመራቅ የታነጸ ነበር፡፡ እዚህ ላይ የኸሊፋው አቡበክርና የዑመረን ታሪክ ብንጠቅስ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

በኸሊፋው አቡበክር ዘመን ዑመር ኢብንል ኸጣብ የበላይ ዳኛ ሆነው ተሾሙ፡፡ አንድም ቀን ከሳሽ ወደቦታቸው ሳይመጣ ሙሉ አመት አለፈ፡፡ በዚይን ጊዜ የኃላፊነት መልቀቂያቸውን ለአቡ በክር አሲዲቅ አቀረቡ፡፡ እሳቸውም ዑመር ሆይ! የዳኝነት ሥራ ስላደከመህ ነው ኃላፊነት መልቀቅ የፈልግሀው? ሲሉ ጠየቋቸው፡፡ ዐመርም አይደለም የአላህ መልክተኛ ኸሊፋ ሆይ! ነገር ግን እያንዳንዱ መብቱን አውቆ ከሱ ያለፈን ነገር የማይጠይቅ፣ በሱ ላይ ያለበትንም ግዴታ አውቆ እሱን ከመወጣት ወደኋላ በማይል ምእምን ማህበረሰብ ውስጥ እኔ ስለማላስፈልግ ነው፡፡ እነሱ ሁሉም ለራሱ የሚወደውን ነገር ለወንደድሙ የሚወድ፣ አንዳቸው በሚሰወር ጊዜ የሚናፍቁት፣ በተማመም ጊዜ የሚጠይቁት፣ በሚደሀይ ጊዜ የሚያግዙት፣ እርዳታ በሚያስፈልገውም ጊዜ የሚረዱት፣ መከራ ሲየሰጋጥመውም የሚያጽናኑት፣ ሃይማኖታቸው ምክርን መለገስ፣ ጠባያቸው በመልካም ነገር ማዘዝና ከመጥፎ ነገር መከልከል የሆነ ማህበረሰብ አባል ስለሆኑ በምን ይካሰሳሉ? በምን ነገር ይካሰሳሉ?› አሉ፡፡

አንድ ሙስሊም ባሪያ በልቡ አላህን ማስታውስ በሚሰፍንበት፣ በምላሱ በሚደጋግመውና አካላቱም ተግባራቸው ባደረጉት ጊዜ መንፈሱ ቀጥተኛ ትሆናለች የአላህንም ውዴታ ያገኛል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) ጸጋውን ይባርክለታል፡፡ ሐዘኑም ይወገዳል ርጋታና የአላህ እዝነትም ያጥለቀልቀዋል፡፡

ጌታችን ሆይ! አንተን በማስታወስና በማመስገንም እገዘን ሀገራችንንም ጠብቅልን ጸጥተዋን ሰላሟን አስከብርልን ሲሳያዋንም የተትረፈረፈ አድርግልን፡፡ አሜን፡፡